የመኖሪያ አድሎ ሕገወጥ ነው፡፡.

“ይህ አፓርትመንት በተሽከርካሪ ወንበር ለሚንቀሳቀስ ሰው የተሰናዳ አይደለም፣ እሱን ለማመቻቸ ለውጦች ማድረግ አልፈልግም፡፡”

“በለቤትህ ነፍሰ ጡር መሆኗን ሰምቻለሁ፡፡ እዚህ ልጆች አንፈልግም፡፡ የኪራይ ውልህ ሲያልቅ ሌላ መኖሪያ ቦታ መፈለግ ይኖርብሃል፡፡”



“እንግሊዝኛህ አይገባኝም፡፡ ማነጋገር ለማልችለው ሰው ማከራየት አልፈልግም፡፡”

በኬምብሪጅ ውስጥ በሚከተሉት ምክንያቶች ለማንም መኖሪያን መከልከል ሕገወጥ ነው፡-

- ✓ የአካል ጉዳት
- ✓ የገቢ ምንጭ (ለምሳሌ ሴክሽን 8ን አልቀበልም ማለት)
- ✓ የቤተሰብ ሁኔታ/የጋብቻ ሁኔታ
- ✓ ዘር/ቀለም/ብሔር
- ✓ ጾታ/የጓደኛ ጾታ ምርጫ/ለእራስ በወሰኑት ጾታ
- ✓ ኃይማኖት
- ✓ እድሜ (18 ዓመት ወይም ከዛ በላይ)
- ✓ የውትድርና ሁኔታ

ከነዚህ ቡድኖች ውስጥ የአንዱ ወይም የብዙው አባል በመሆናቸው ምክንያት ትክክለኛ ያልሆነ መስተንግዶ የሚያገኙ ሰዎች በ Fair Housing Laws (ትክክለኛ የመኖሪያ ሕጎች) የተጠበቁ ናቸው፡፡

እርስዎ ወይም የሚያውቁት ሰው የመኖሪያ አድሎ ካጋጠምዎት የ Cambridge Human Rights Commission ጋር አሁኑኑ በስልክ ቁጥር (617) 349-4396 ይደውሉ፡፡

Human Rights Commission Cambridge

የሚከተለውን እናደርጋለን፡-

- ✓ አቤቱታውን መመርመር
- ✓ አድሎ እንደተፈጸመ ከደረስንበት፣ በአስታራቂነት የፈቃደኝነት ስምምነት ለመድረስ መሞከር
- ✓ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ሕጋዊ ችሎት ተደርጎ የገንዘብ ካሳ፣ ቅጣት ወይም ሌሎች እርምጃዎች መውሰድ ይቻላል

የCambridge Human Rights Commission እርስዎ ላይ የተከሰተው ሌላ ማንም ላይ እንዳይከሰት ለማድረግ ይሞክራል!

የመኖሪያ አድሎ ምንድን ነው?

☑ ጥበቃ ይለው ቡድን አባል በመሆንዎ ምክንያት የሚከተሉት እርምጃዎች ሲወሰዱ ፦

መኖሪያ መኖሩን በተመለከተ ትክክል ያልሆነ መረጃ መስጠት፦ አንድ አፓርትመንት፣ ቤት ወይም ኮንዶሚኒየም እያለ አንድ አስተዳዳሪ፣ ባለቤት ወይም የቤት አሻሻጭ የለም ሲልዎት።

ለማከራየት ወይም ለመሸጥ ሲከለከል፦ አንድ አስተዳዳሪ ወይም የቤት አሻሻጭ ለእርስዎ አላከራይም ወይም አልሸጥም ሲል።

በስምምነትና ደንቦች ላይ አድሎ ሲደረግ፦ ከሌሎች የተለየ ደንብ ወይም ሥርዓት ሲሰጥዎ።

አግባብ ያላቸው የመኖሪያ ሁኔታዎች ሲከለከል፦ አንድ የአካል ጉዳት ያለበት ሰው አንድ አፓርትመንትን ለመጠቀም እንዲያስችለው የሚያስፍልገውን ከፖሊሲ ለወጥ ያለ ነገር አላደርግም በማለት አንድ አስተዳዳሪ ሲከለክል።

አበዳሪዎች ወይም ዋስትና ሰጪዎች አድሎ ሲያደርጉ፦
የቤት ብድር፣ የቤት ባለቤት ዋስትና ወይም የተከራይ ዋስትና ለማግኘት ወይም ማመልከቻ ለማስገባት ሲታገዱ።

የመኖሪያ አስተዳዳሪዎች፣ ሻጮችና የቤት አሻሻጮች አመልካቾችን የሚያስተናግዱት ገለልተኛ በሆኑ መስፈርቶች፣ ለምሳሌ የመክፈል ችሎታ ላይ ተመሥርተው መሆን አለበት። እነዚህ መስፈርቶች ለሁሉም እኩል መሆን አለባቸው። አድሎ ብዙ ዓይነት መልክ አለው።

የሚከተሉትን ማድረግ ሕገወጥ ነው፦

- » አንድ ሰው ክፍት ለሆነ መኖሪያ ቦታ ማመልከቻ እንዳያስገባ ማዳከም ወይም መከልከል
- » አንድ ቤት ለምርመራ፣ ሽያጭ ወይም ኪራይ አይቀርብም ብሎ በሐሰት መከልከል
- » ለአንድ መኖሪያ ቦታ ከሌላው ከፍተኛ የሆነ የኪራይ ወይም የሽያጭ ዋጋ ማስከፈል ወይም መንገር
- » የመንግሥት እርዳታ ለሚያገኝ አመልካች አላከራይም ማለት (ሴክሽን 8ን ጨምሮ)
- » የቤቱ ቀለም እርሳስ (ሌድ) ስላለው ልጆች ላለው ቤተሰብ መኖሪያ አልሰጥም ማለት
- » በማስታወቂያ፣ በጽሑፍ ወይም በቃል ንግግሮች ላይ አድሎ ማንጸባረቅ
- » አንድ ግለሰብ የተጠበቀ ቡድን አባል ስለሆነ ማስፈራራት፣ ማስገደድ ወይም ማስጨነቅ
- » አንድ ግለሰብ የትክክለኛ መኖሪያ መብቶቹን ስላስከበረ አጸፋ መመለስ
- » አንድ ሰው የአካል ጉዳት ስላለው አግባብ ያለው ማመቻቸት አለማድረግ ወይም ማዳላት
- » የንብረት ሽያጭን ለማሟሟቅ የዘር ለውጥ አሉባልታ ማስፋፋት
- » ለተወሰኑ ሠፈሮች የቤት ግዢ ብድር ወይም ዋስትና መከልከል

Human Rights Commission Cambridge

የCambridge Fair Housing Ordinanceን (የካምብሪጅ ትክክለኛ መኖሪያ ድንጋጌ) ሙሉ ጽሑፍ ለማየት እባክዎን ድህረ ገጻችንን ይጎብኙ፦
www.cambridgema.gov/HRC
ወይም በስልክ ቁጥር (617) 349-4396 ይደውሉ።

EQUAL HOUSING OPPORTUNITY

የዚህ የታተመ ጽሑፍ ሥራ ድጋፍ ያገኘው በ U.S. Department of Housing and Urban Development (ከዩ ኤስ የመኖሪያና ከተማ ልማት) ጋር ባለ ስምምነት ሥር ካለ የገንዘብ እርዳታ ነው። የሥራው ግኝቶች ለሕዝቡ ይውላል። በዚህ የታተመ ጽሑፍ ውስጥ የሚገኘው መረጃ ትክክልነትና ትርጉም ሙሉ በሙሉ የጸሐፊውና የአታሚው ኃላፊነት ነው። እነዚህ ትርጉሞች በግድ የመንግሥቱ አቋምን አያመለክቱም።